# *ማን ያውራ የነበረ 10*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮና ቆርጦ ለትግል ከተነሳ ኃያልና አቸናፊ መሆኑን ለዓለም ሁሉ ግልፅ ያደረገበት አንዱ ጊዜ በየካቲት 66 ነው፡፡ ከሰላሳ  አንድ ዓመት በፊት መሆኑ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያን ቀስፎና አላሳድግ ብሎ የያዘ ኋላቀርና በአፄ የሚመራ ስርዓት ነበረ ፡፡ ይህ ስርዓት የማይደፈር የማይነካ መስሎ ለንጉሱ የስልጣን ማጠየቂያ "ስዩመ እግዚአብሔር" የተባለውን ለብሶና በ"አፄው ምን አጠፉ ሕዝብ ጠግቦ እንጂ" ባይ ባለሚሎች ታጅቦ ዘለዓለማዊነት ቃጥቶት ነበር፡፡ ንጉሱ የለውጥን ጥሪ ደወል መስማት አቅቷቸው የተሞከሩባቸውን መፈንቅለ መንግስቶች ቢቋቋሙም በየካቲት እያስገመገመ የመጣውን የለውጥ ጎርፍ ግን ሊረዱትም ሆነ ሊያመልጡት አልቻሉም፡፡*

*የካቲት 66 በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ከፍተኛ ቦታ የያዘ የአብዩት ክስተት ነው፡፡ ኢሕአፓና የካቲት 66 የማይነጣጠሉ ናቸውና አብዮቱን አመጣብን ብለው ለሚከሱት መልሱ እንዴታ እንጂ አጥፍቻለሁ አይደለም፡፡ የየካቲት አብዮት ለኢሕአፓና ለሌሎች አንድ ዓይነት ትርጉምና አንደምታ የለውም፡፡ <u>ኢሕአፓና የካቲት 66</u> ሳይነጣጠሉ የሚቀርቡ የታሪካችን አካል የሆኑትም በትግል እንጂ በሌላም አይደለም፡፡ በየከቀቲት 66 የፈነዳው የሕዝብ አመፅ ለዓመታት ቦግ እልም ቦግ እያለ ሲካሄድ የነበረው የጭቁን ሕዝብ ትግል ውጤት ነው፡፡ የላብ አደሩ፣ በጎጃም፣ በባሌ ወዘተ የነበረው የገባሩ አመፅ፣ የተማሪውና ምሁሩ ቆራጥ ትግል ወዘተ... ተጠራቅሞና በፈሰሰ የሰማዕት ደም ኃይልን አግኝቶ የየካቲት 66  ዓመፅ ወለደ ፡፡ ያኔም እንዳሁኖቹ የጠገበና ጉም ልጨብጥ ያለ ህሊና ቢስ ገዢ መደብ ነበር፡፡ አርሶ አደሩ ለጪሰኝነት ተዳርጎ፣ ሰፊው ሕዝብ እየተበዘበዘና ለድህነት ተሰጥቶ፣ የሀገር ሉዓላዊነት ተደፍሮ፣ በሃይማኖትና በብሄረሰብ የተነሳ ልዩነት ሰፍኖ ነበርና ማለትም በደልና ጭቆና ነበርና የሕዝብም አመፅ መቀስቀሱ አልቀረም፡፡ ተማሪዎች ያስተማራቸውን ሕዝብ ብሶት ሰምተው ለውጥ ይምጣ ብለው ተነሱ እንጂ ሀገር ሰላም ሕዝብ ደስተኛ ሆኖ ባለበት ሁኔታ ያኔ ይባል እንደነበረው ዕንቁላልና ቲማቲም በልተው ጠግበው ወይም ብስኩትና ወይን ይሰጧቸው የነበሩት አፄ ላይ በባዕድ ቀስቃሾች ተገፋፍተው ተነስተው አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን እንድታድግ፣እንድትበለፅግ የሚፈልግ ሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ፣ መብትና ዴሞክራሲን የሚሻ ሁሉ ከአፄው ስርዓት ጋር መጋጨቱ የግድ ነበር፡፡ ዛሬ በአደባባይ የአፄውን ምስል ሰቅለው ኃይሌ ኃይሌ ባዮች የስርዓቱ ሰለባ  ስላልነበሩ አሌ እንደሚሉን ብናውቅም ሀቁ ግን የአፄው ስርዓት የበሰበሰና መወገድም የነበረበት መሆኑ ነው፡፡ የካቲት 66 በራሱ ላይ ያመጣው ስርዓቱ ራሱ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡*

*የካቲት 66 ለኢሕአፓ የመርህና እምነቶቹ ምስክር ሆኖሎታል፡፡ ጭቁን ሕዝብ ከተባባረ የታጠቀን ኃይል ሊያሸንፍ እንደሚችል የነበረውን እምነት አረጋግጦለታል፡፡ ተማሪ፣አስተማሪ፣ ታክሲ ነጂ፣ነጋዴ፣ ጭቁን ሴቶች፣ የቢሮ ሰራተኞችና ወታደሮች ሁሉም በሂደት አብረው ሕዝባዊ አመፅ በማካሄድ ግባቸውን አግኝተዋል፡፡ ዛሬ ስለ  ሕዝባዊ አመፅ እያወሩ ግን "እስርና ሞት ባይኖር አመፁ ባልከፉ" ባዮች በበዙበት ይህንን የየካቲት 66  ትምህርት ዳግም ማጤን የግድ ነው፡፡ አብዮቱ አብዮት የሆነውና ድልንም ያገኘው በመስዋዕትነት ነው፡፡ ብዙ ህይወት ጠፍቶ፣ ለትግሉ ተገብሮ ነው፡፡ የካቲት አብዮት የእኔ ብጤው ጭቁኑ ሁሉ መድረኩ የእኔ ያለበት ስለነበር የትግል ማዕከል የጉባዔ  ወይም የፓርላማ አዳራሽ ሳይሆን ባቡር መንገዱ፣ሼራተን ሂልተን ሳይሆን መርካቶ ነገሌ ነበር፡፡ ታሪክ ሰሪውና ተራ የተባለው ዜጋ ማንነቱን ያሳየበት ታሪካዊ ወቅት ነበረ ፡፡ ትግሉን በመጨረሻ የታጠቀ ኃይል ቢያደናቅፈውም በሂደቱ ወቅት ፍሬን ያዝ ሊሉትና ሊያቆሙት የጣሩትንም ደግሞ እያሳፈረ ዛ    ግድያ ሳይገታው ወደፊት ገስግሷል፡፡*

- *ለነበረው ስርዓት ተጠቃሚዎችና ሎሌዎች የካቲት 66 ተራማጁ ወጣት ያመጣው ዱብ ዕዳና መርገም ነበረ፡፡ ስለዚህም ሲረግሙትና በዚያውም መሰረት ተጠያቂ የሚሉትን ኢሕአፓንም ሲያወግዙ ቆይተዋል፡፡*
- *ለጠባቦችና ገንጣዮችም የየካቲት አብዮት የሕዝብን አንድነት የገለጠና በገቢር ያሳየ፣ ሕዝቡ በአንድ አይኖርም ያሉትን ያሳፈረ ፀረ ጠባብ ክስተት ነበረና ዛሬ ለይስሙላ ቢያወድሱትም ይዘቱና መልዕክቱን ግን ተቃውመው ይገኛሉ፡፡*
- *የታጠቀ ገዢ መደብ በሕዝብ አይሸነፍም ያሉና የጭቁኖችን ትግል የ  ቁም አፍረዋል፡፡*
- *ሕዝብ የሚያታግለው ካገኘ ፣ አብረውት ሞትን የሚደፍሩ ጀግኖች ካሉ የማይገረሰስ የተባለውን ሁሉ ገርስሶ ሊጥል እንደሚችል አሳይቷል፡፡*

- በዚሁ መሰረት ደግሞ ሕዝብ በሚገባ ካልተደራጀ ፤ ብቁ መሪ ድርጅት ከሌለው፤ድሉን ማስከበሪያ ሳይል ከሌለው ድሉን ሊነጠቅ እንደሚችልም ታይቷል፡፡
- የሰራተኛው ሕዝብ የትግል መሳሪያ የሆነውን የስራ ማቆም አድማ ተማሪውም ታክሲ ነጂውም፤የቢሮ ሰራተኛውም የአየር መንገዱም፤የባቡር፤የትራንስፖርቱም ሰራተኛ ወዘተ ሁሉም ከተጠቀመበትና በተለይም ጠቅላላ የስራ ማቆም አድማ ከተደረገ  መንግስት ተብዬን ማንኮታኮት እንደሚቻልም ተረጋግጧል፡፡
- ሁሉም በየፊናው ወይም ዛሬ ወያኔያዊ መዝግበ ፖለቲካ በጫነብን ፈሊጥ በየክልሉ ተወስኖ የራሱን ብሶት ብቻ እያሰማ፤ ከብሄረሰቤ ሌላ የቀሪው ጉዳይ አያገባኝም እያለ ፤ ተነጣጥሎና ተለያይቶ ለገዢዎች አመችቶ የታገለ ሳይሆን አንዱ የሌላውን ጥያቄ እየደገፈ በጋራ በኢትዮጵያዊነት በእስልምና ሀይማኖት ተከታዮቸች ሰልፍ ላይ ክርሰቲያኑም እየተገኘ፤ የሴቱንም ሰልፍ ወንዱ እየደገፈ ፤የአስተማሪም ጥያቄ ተማሪውና ሌላውም እያስተጋባ፤የሰራተኞችን አድማ ሁሉም እያጀበ ወዘተ በጋራ ታግሎ ፍሬን አግኝቷል፡፡

በአሁኑ ጊዜ አዲሱ ትውልድ በተለይም ወጣቱ ለየካቲት አብዮት ባዳ ነው፡፡ ስልጣን የያዘው ደርግ እንኳን ከወደቀ 14ኛ ዓመት እነሆ እየመጣ ነው፡፡ ለዚህም ነው የአብዮቱን ታሪክ የሚበርዙ ዛሬ ፈልተዋልና የዚያን ታሪካዊ የሕዝብ ትግል ይዘትና ዓላማ ለአዲሱ ትውልድ ማስተማር ማሳወቅ ግዴታችን መሆን ያለበት፡፡ ዛሬ ድርጅቶች አንድ አሸን ፈልተዋል፤ ከተከለከሉት በስተቀር ብዙዎቹም ህጋዊ ተብለው በይፋ እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ ሀገሪቷ ደግሞ ወደ ባሰ መከራና ስቃይ ወረደችና በተሻለ ሁኔታ ላይ አትገኝም፡፡ ሕዝብ ተበደልኩ ብሎ ዛሬም ይጮሃል፡፡ታዲያ የሕዝባዊ አመፅ ደብዛው ለምን ጠፋሳ ብለው ለሚጠይቁ አንደኛው መልስ የሚሆነው ወደ ኋላ መለስ ብሎ የየካቲትን አብዮት ይዘትና ሂደት መመርመር ይሆናል፡፡ የተዘባነኑና ባለነፍጥ ገዢዎች ነበሩ/አሉም፡፡ የከፋ ጭቆና ነበር/አለም፡፡ ያውም ዛሬ ብሶ ሀገር ራሷ ለቅርጫ ቀርባለች፡፡ ድርጅቶች ያኔ ገና ብቅ ማለት ጀማሪና ህቡዕ ነበሩ/ዛሬ ድርጅት በዝቷል፤ በይፋ ይንቀሳቀሳል፡፡ ታዲያ ዛሬ ምነው ሕዝባዊ አብዮት እውን አልሆን አለ ለሚለው ጥያቄ ያው ምላሽ ለመስጠት የታሪኩ ተመክሮ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለባዕዱ ችግር ፈጣሪነት ከሆነ ያኔም ነበረና በቂ ሽፋን ሊሆን አይችልም፡፡ ማን ዓይነት ድርጅት፤ምን ዓይነት የትግል መሪዎች፤ምን ዓይነት ትግል የሚሉትም መመለስ ሊኖርባቸው ነው፡፡ የካቲት 66 በተዓምር የተወለደ ሳይሆን የዓመታት ትግል ድምር ውጤት መሆኑን አለመርሳትም ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ ትግል የነበሩና የተሳተፉት ግንባር ወይም ክፍሎች ደግሞ የሕዝብን መንፈስ ከሚገድሉ፤ወኔን ከሚያቀጭጩና ቀቢፀ ተስፋን የበላይነት ከሚሰጡት ጋር ሁሉ ታግሎ በማቸነፍ ድፍረትን ተላብሶ፤ይቻላልን መፈክሩ አድርጎ፤ ትግል የማያፈርሰው የጭቆና ግምብ የለም በማለትና በሕዝብ ታሪክ ሰሪነት ሙሉ በሙሉ በማመን የታገሉ ነበሩ፡፡ ሹመት ሹመቱን ስጡኝ ትግሉን ግን ለሌላ የሚሉ አልነበሩም፡፡ ገዢውን ክፍል ወይም መንግስት ተብዬውን የሚፈሩ አልነበሩም፡፡

ይህ ድፍረትና ጀግንነት ከታሪካችንም ሊገኝ የሚችል ቢሆንም እምነት መኖሩ ደግሞ ወሳኝ ነው፡፡ ዛሬ ያወቁ መስሏቸው ራዕይ አያሻም፤የፖለቲካ ርዕዮት መኖሩ አይጠቅምም ወዘተ የሚሉ አዋቂ ነን ባዮች ቢበዙም የትግልን ግብ ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ለትግሉ የሚያሻውን ድፍረት፤ ወኔና ፅናት ለመያዝም ራዕይ፤የፖለቲካ እምነት፤ አንቀሳቃሽ ርዕዮት መኖሩ የግድ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ በ1982 የወጣው ዴሞክራሲያ ቅፅ 16 ቁጥር 2 ያሰፈረውን መጥቀስ ቦታው ነው፤

" በጥንታዊ ስልጣኔዋ፤በነፃነት ዓምድነቷ አሻቅበው የሚያይዋት፤የሚኮሩባት፤ተገን ወገን የምትሆን ሀገር መሆኗ ቀርቶ የመጨረሻይቷ ኋላቀር፤ነዳይ ምስኪንና ምፅዋተኛ፤የሁከት መናኸሪያ፤የእድገት መቀበሪያ ሆና፤ቁልቁል በአፅንዖና ዓይንን ሰብሮ ስለሚመለከቷት፤ትቢያ ላይ ስለወደቀች ሀገር ቁጭት ለሚሰማው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የኀዳውን ጣጣ ፈንጣጣ፤የግሉን አንጃ ግራንጃ ወደ ዳር ትቶ፤ ትቢያዋን አራግፎ፤ርስህቷን ከልቶ፤ በትር ምርኩዝ ሆኖ በእግሯ ተደላድላ እንድትቆም አድርጎ ሀገር አለሻ ለማለት መብቃት የቀረበለት ቁልጭ ያለ የሞት ሽረት ጥያቄ ነው፡፡ከዚሁ ሀገርን እንደ ሀገር ከማቆም ጥያቄ ጋር አብሮ መመለስ ያለበት ይህችው ሀገር ቆማስ ወዴት ነው፤በምንድነው የምትራመደው የሚለውም ጭምር ነው፡፡ ኢትዮጵያ ጤና እንድትገዛ፤ሕዋሳቷ ሕይወት አግኝተው እንዲነዝሩ፤ እጆቿን ወደ ጥበብ አድማስ እንድትዘረጋ፤ ያለ መሰናክል በእድገት ጎዳና እንድትራመድ ኋላ የቀረችውን ያህል እንደትገሰግስ፤አመንምኖ ከዚህ ድቀት የጣላትም… ዳግመኛም የማይመለስብትን መላ መምከር የግድ ነው፡፡"

መላ አልነው ራዕይ ውይም ርዕዮት የምናምንበትና ሕይውት ሳይቀር ልንሰዋለት የምንችል እምነት ያስፈልገናል:: ያለፈው ታሪክ የሰራ ትውልድ ይህ ዓይነት ርዕዮትና እምነት ነበረው:: የትግሉ ነው ህይወቴ ብሎ እየዘመረ ሞትን የተጋፈጠው ህይወቱን ጠልቶ ወይም ተታሎ ሳይሆን በመርሁ አምኖ ነው:: ይታገል የነበረው ለሹመትና ለግል ጥቅም ሳይሆን፤ለገንዘብና ለዝ ሳይሆን ለሀገርና ለሕዝብ ስለነበርም፤ ቃሉና ቃልኪዳኑም የይስሙላ ሳይሆኑ የልቡ ስለነበሩ ላመነበት በቆራጥነት ታግሏል:: ዛሬ የትግል መሪ ነን የሚሉትና እያካሄድን ነው የሚሉትን "ፈልጉኝ በመብራት" ትግል ስናወዳድር ደግሞ ችግራችን የት ላይ እንደሆነ የምንስተው አይደለም:: በክልል ከተወሰንን፤ ተማሪው በጋራ በመነሳት ፈንታ በብሄረሰብ ተከፋፍሎ ከተናቆረ፤ ድርጅቶች የታጋይ ድርጅትን ምንነት ገና ማወቅ ያቃታቸው ከሆኑ፤ ሩጫው ለሹመት ከሆነ፤ ገዢ ተብዬው ከተፈራ፤ ምሁሩ በጥቅም ተገዝቶ ከተልፈሰፈሰ ፤ ባዕድ ነፃ ያወጣናል ተብሎ ከተጠበቀ፤ ትግል ሳይሆን ስለ ትግል ማውራቱ ከበዛ፤ መድፈር ከቶም ካቃተ ፤ ወኔ ስደት ከሄደ ወዘተ የሀገር ፍዳ በአጭር ጊዜ የመቆም አይሆንም:: የካቲት 66 የሚሰጠው ትምህርት ይህ ነው::

ወያኔና መሰሎቹ ነፍስ የዘሩት የካቲት 66 ሲመታ፤ የመኮንኖቹ ቡድን ስልጣን ሲይዝ፤ ለዴሞክራሲ የታገሉት ኢትዮጵያዊ ኃይሎች በተለይም ኢሕአፓ በሽብር ሲጠቃና ሲዳከም መሆኑ ራሱ የሚያመለክተው ያ ቀና ጎዳና ተዘግቶ አጥፊው መንገድ ግን መጠረጉን ነበር:: ዛሬ ወያኔ ሕዝብን በክልል ከፋፍሎ፤ ድርጅት የተባሉትም የብሄረሰብ ሆነው፤ የሀገር አንድነት መንፈስ ሳይሆን የብሄረሰብ ክፍፍል መጥፎ አየር እየነፈሰ ባለባት የካቲትን ለመድገም ጥረቱ ቀዳሚ መሆን እንዳለበት ግልፅ ነው:: ጨቋኝን ታግለው ያንበረከኩታል እንጂ አይለማመጡትን መልዕክት የካቲት 66 ሰጥቶን አልፏል:: ሕዝባዊ አመፅን ማደራጀት ይቻላል ብቻ ሳይሆን የግድ ነው ማለትም አለብን:: አመፅ ማደራጀት ብቻ ሳይሆን የመለስን አገዛዝ አንኮታክቶ መጣልም ይቻላል:: ይህ መታመን አለበት:: ከታመነበትና ከሀገር በላይ ሁሉም ዋጋ ቢስ ነው ከተባለ ለኢትዮጵያ ስንል መሰዋት እንደፍራለን ማለት ነው:: ለወያኔ ምርጫ ለመመዝገብ ከመዋደቅ በፊት ሕዝባዊ የተቃውሞን ሰልፍ ለማደራጀትና ለመመምራት እንፎካከራለን ማለት ነው:: ውድድራችን ማነው የዳዊት ዮሐንስንና የመለስ ዜናዊ ማላገጫ ለመሆን ከወያኔ ፓርላማ የሚገባ ሳይሆን ማነው የሕዝብን ትግል መርቶ በጀግንነቱና በወኔው ለሕዝብ አርአያ ለሀገር የሚያኮራ የሚሆነው በሚለው ላይ ይሆናል:: የካቲት 66 ስንል ይህን ሁሉ አጢነን ነው:: በደርጉ መውደቂያ አዝማምያም በወጣውና ከላይ በጠቀስነው ዴሞክራሲያ ያኔም ቢሆን ዓቅምን በውል እንጠቀም በሚል እንደሚከተለው ቀርቦ ነበር፤

" በየካቲት 66 ዓ.ም. ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ አንድ ሰው ቁሞ፤አንድ አንደበት፤ አንድ የተባበረ ኃይል ሆኖ ያመጣው ለውጥ የጦርነት፤የሁከት፤ የግፍ የጭቆናን መሰረት ለመናድ ቢቃጣውም፤ በአዲስ መልክ ተደራጅተው የመጡበትን የዓመፅ ኃይላት አቸንፎ የሕዝብ መቅሰፍትን፤የሀገር ውርደትን ሊያስቀር አልተቻለውም:: ያልተቻለው ዓቅም አንሶት ሳይሆን፤ ዓቅሙን በውል ለመጠቀም የሚያስፈልገውን ቅንጅት ለማድረግ፤ አካሄዱን ለመትለም ስለተሳነውና ይህም ድክመቱ ለጠላት ብርታት ጉልበት በመሆኑ ነው:: ይህንን ድክመቱን በርትቶ ለማስወገድ እስካልተቻለውም ድረስ የጥፋት ዘመኑን ፈፅሞ ሰበን መገነዙን በማዘጋጀት ያለውን ፋሽስታዊ መንግስት አሳልፎም የከፋ ሁከት ውስጥ መዘፈቅና የሕዝብ አንድነት የሀገር ምንነት ከጥያቄ ላይ የሚወድቅበት ሁኔታ ሊከተል ይችላል::"

አደጋው መከሰት ብቻ ሳይሆን በከፊልም ሊሳካ ችሏል:: ሀገረም ተጎድተቀለች፤ኢትዮጵያዊነትም ተቋቅቶ ማንነታቸውን የካዱ ጉዶች ፈልተውም ነበር:: አቅምን ማቀናጀት የየካቲት አብዮት ፀጋ ነበር:: የተባባረና ያበረን ማፍረስ ደግሞ የዛሬ ብልህ ፖለቲካ ተብሏል:: ጉልበታችን የዛለውም ለዚህ ነው:: በህብረት በመቆም ፈንታ የተባባርን መከፋፈል የተማርን ባዮቹ፤ የዶክተር ፕሮፌሰር በሉን ባዮቹ ተልዕኮ ሆኗል:: ብረት ያነሳውን ጦሮዮ በሎ ማውገዝ፤ሰላም ካለችሁ ሕዝባዊ ሰላማዊ አመፅን ማካሄድ ላይ እናተኩር የሚለውን ማደናወፍ ማውገዝ እንዲያው ብቻ ስል ትግል እያወሩ መሞሸርና ከገዢዎች ጋር መሞዳሞድ በዝቷል:: ርዕዮት ወይም ህዝባዊ ራዕይ የለም፤ እምነት የለም፤ ሀቅ ለችርቻሮ ቀራቢ ነው፤ ቡከንነት አያሳፍርም፤ለሹመት መግንበስስ ደግሞ ትግል ተብሏል:: የካቲት 66 ዛሬ ቢያንስ ከፖለቲካ ድርጅቶች የትግል መንፈስ አንፃር በጣም የተለያዩ ናቸው::ማን ያውራ የነበረ ስንልም ያኔም ቢሆን ከትግሉ ጎራ ወደ ጨቀኙ ና ወደ ባለ ነፍጥ ያደሉትን የምናውቃቸው ስለሆነ ለእኛ አብዮቱ ፀጋ ለእናንት ገን መርግም ነበር ብለን ልናስታውሳቸው በመፈለግም ነው::

ጨቋኝ ስርዓቶች በሕዝብ ትግል መውድቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ ይህ ግን የድንገት ዱብ ዕዳ አይደለም፡፡  ትግልን ይጠይቃል፡፡ በጥሩ ሁኔታ ለመታገል ደግሞ ዓቅምን ማቀናጀት፣ማበር መተባበር ያሻል፡፡ ለህገር በአፍ ሳይሆን በተጨባጭ መታገል የግድ ይሆናል፡፡ ትግል ሲባል ደግሞ በህይወትም በሌላም ዋጋ የማይከፈልበት ትግል ቢያንስ ለእኛ የሚታወቅ አልሆነም፡፡ከገዢዎች ጋር ተግባብቶ መታገል ትግል ሳይሆን መለጠፍ ነው፣ለጨቋኝ ተባበሪና ሎሌ መሆን፡፡ በየካቲት ይህ በሕዝብ ጎራ አልተከሰተም፣ብቅ ቢልም ተቀጭቷል፡፡ ሕዝብ እዚህ ላይ ሚናው ዋነኛ ነው፡፡ አድርባዩንና የጨቋኞችን አጎብጓቢ ማራቅ መነጠል አለበት፡፡ ኢሕአፓና የየካቲት አብዮት የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ የየካቲት ድል በመኮንኖች ሲቀማ ለማስመለስ የተዋደቀውና የሽብር ሰለባ የሆነው ኢሕአፓ ነው፡፡ ዛሬ ኢሕአፓ በሀገሩ ህገወጥ ትብሎ ይጠቃል፣ይሳደዳል፡፡  የካቲት 66 ያስወገደው ስርዓት አባወራዎች ግን በሀገር ቤተ ነፃ ሆነው፣ንብረት አስከብረው ይንፈላሳሳሉ፡፡ ዛሬ የኢሕአፓ ሀቀኛ አባላትና መሪዎች ወደ ሀገር መግባት ወይም በሀገር ይፋ መውጣት አይችሉም፡፡የካቲትን ያፈነው ስርዓት ቀንደኞች ግን የአሁኑን ገዢ መደብ ደጋፊና አማካሪ ሆነው  ይንደላቀቃሉ፡፡ ኢትዮጵያ የሞተላት ሳይሆን የገደላትንና ሊገድላት የሚሯሯጠውን የምታቅፍ ሀገር መስላ አንዳንዴ ብታበሳጭም የያከቲት 66 አብዮት ግን ሕዝቧን የማትረሳና ጨቋኞችን የምትቀጣ መሆኗንም አሳይቷል፡፡

ኢሕአፓ የየካቲት አብዮትን በተመለከተ ሆነ ከዚያም በኋላ የየካቲትን መርህ ላመስከበር ባደረገው ትግል ይኮራል፡፡ ዛሬም ቢሆን ሕዝባዊ ለውጥ በየካቲታዊና ነጎድጓዳዊ ትግል የሚወለድ ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምን አድርባይነትን የፖለቲካ ብስለት ብሎ ከአገዛዙ የገማ ሸበጥ ወይም ጫማ ስር ለመነጠፍ ማንነቱና የሰማዕት ደም መቸም አይፈቅዱለትም፡፡

የየካቲት 66 አብዮት በወያኔ ላይ ይደገማል!!!